በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 1.0/558/08
Ref. No.
ቀን 22 ግንቦት 2008
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

በያሉበት

ጉዳዩ፡ የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈጻም የወጣ መመሪያ ቁጥር 117/2008 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ የላክንላችሁ ስለሆነ መመሪያው ተግባራዊ እንዲደረግ አሳስባለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ሙሉ ገብረ እግዚአብሔር [illegible]
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- አገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም፣ ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት ስራዎች ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ታክስ ፕሮግራም፣ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለህግ ጥናት፣ ረቂቅና ዝግጅት ስልጠና ዳይሬክቶሬት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ/ Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ዳይሬክቶሬት

- ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለየታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለወንጀል ምርመራ ዳይሬክቶሬት
- ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ
- ለአ.አ. ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለፌዴራል ወንጀልና ፍትሐብሄር ጉዳዮች ክትትል ዳይሬክቶት
- ለህግ ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለህግ ምክርና አስተያየት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት
- ለድንበር አስተዳደርና ኮንትሮባንድ ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለዕቅድና አፈጻጸም ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለየተያዙና የተወረሱ ንብረቶች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት አሰራር ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ስራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥ ትግበራ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍና ትብብር ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለአዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶች ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለትምህርትና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን ኦዲት የስራ ሂደት
- ድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ፕሮግራም ልማት ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለሀብት አስተዳደር ቢሮ

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመርካቶ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- መርካቶ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 1 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቁጥር 2 መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለቂርቆስ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአራዳ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለየካ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለልደታ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- አዲስ ከተማ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት /አዳማ/
- ለሞጆ ቅ/ጽ/ቤት /ሞጆ/
- ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ባህርዳር/
- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /መቀሌ/
- ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ድሬደዋ/
- ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሚሌ/
- ለጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅግጅጋ/
- ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ሞያሌ/
- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት /ጅማ/
- ለጋላፊ ቅ/ጽ/ቤት /ጋላፊ/
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት /ኮምቦልቻ/
- ሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት /ሐዋሳ/

# የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ

## ቁጥር 117/2008

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

2008 ዓ/ም

# የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 117/2008

የገቢ፣ የወጪ፣ የአገር ውስጥ እና የተላላፊ ዕቃዎችን የጉዞ መተላለፊያ መስመር በሕግ መወሰንና ከተወሰነው መንገድ ውጭ የሚጓጓዙ፣ የሚቆሙ፣ የሚያራግፉና የሚጭኑ አጓጓዦችን ለመቆጣጠር እና ሕጋዊ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በገቢ እና በወጪ ዕቃዎች ላይ አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ፣ የመተላለፊያ መንገዶች ላይ በሚደረገው የቁጥጥር ስራ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ኃላፊነትና ግዴታ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የትራንዚት ዕቃዎች የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለባቸዉን ቅድመ ሁኔታዎች በመወሰን፤ ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የትራንዚት ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የትራንዚት ፍሰቱን ይበልጥ የተሳለጠ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ባለሥልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 16(4) ፣18(3)እና (5)መ፣ 19(1)፣ 21(3)፣ 22(4) እና 180(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 117/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

   1) "የትራንዚት ዕቃ" ማለት የጉምሩክ ሥነ- ሥርዓት ያላጠናቀቀ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ በተፈቀደ መስመር የሚጓጓዝ ዕቃ ሲሆን በባለስልጣኑ በተፈቀደ ቦታ የሚጫንና የሚራገፍ ዕቃን ይጨምራል፡፡
   2) "የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም" ማለት የትራንዚት ዕቃ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆኖ ከጉምሩክ መነሻ ጣቢያ እስከ መድረሻ ጣቢያ ወይም ወደ/ከተፈቀደ ቦታ የሚተላለፉበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሂደት ነው፡፡
   3) "የትራንዚት መነሻ ቦታ" ማለት የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት የሚጀምርበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም የተፈቀደ ቦታ ሲሆን በአጎራባች አገራት ያሉ የባለስልጣኑን ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

4) "የትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታ" ማለት የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ስርዓት የሚያበቃበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም የተፈቀደ ቦታ ነው፡፡

5) "የትራንዚት መግቢያ ቦታ" ማለት የትራንዚት ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል ተጓጉዞ የሚገባበት በር ነው፡፡

6) "የተፈቀደ ቦታ" ማለት ከጉምሩክ ጣቢያ ውጭ የትራንዚት ዕቃ እንዲራገፍበት ወይም እንዲጫንበት በባለስልጣኑ የተፈቀደ ስፍራ ነው፡፡

7) "ዋና መንገድ" ማለት የመንገድና ትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና መንገድ ብሎ የሚወስነዉ መንገድ ነዉ፡፡

8) "የጉምሩክ ማሸጊያ" ማለት የትራንዚት ዕቃ ደህንነት ለመጠበቅ የሚያገለግልና የትራንዚት ዕቃዎች መያዣ ወይም ማጓጓዣ ላይ የተጫነ ዕቃ የሚታሸግበት ወይም የሚታሰርበት በባለስልጣኑ ዕዉቅና የተሰጠዉ መሳሪያ ነው፡፡

9) "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት አጓጓዡ በጉምሩክ ትራንዚት ኦፕሬሽን ወቅት ትራንዚት ዕቃን ለጉምሩክ ትራንዚት ኦፕሬሽን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ እና ሁኔታ የትራንዚት መድረሻው ቦታ ላይ እንዳይደርስ ምክንያት የሚሆን እና አግባብ ባለው ህግና በአለም አቀፍ ስምምነት ተቀባይነት ያለው ከአጓጓዡ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ክስተት ነው፡፡

10) "ከአቅም በላይ ለሆነ ሁኔታ የሚቀርብ ማስረጃ" ማለት በጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ስርዓት አፈፃፀም ወቅት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የገጠመው አጓጓዥ ሁኔታውን በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም ህግ አስከባሪ አካል/የአካባቢ መስተዳደርን ጨምሮ/ አስታውቆ ከዚሁ አካል ስለ ሁኔታው የተሰጠ የጽሁፍ ማረጋገጫ ነው፡፡

11) "ፖትሮሊንግ" ማለት ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ለመጓዝ የትራንዚት ፈቃድ ያገኙ፤ እንዲሁም ከወደብ እና መግቢያ በሮች የሚንቀሳቀሱ ትራንዚት ዕቃዎችን መረጃ በማጠናቀር አስቀድሞ በተነደፈ መርሐ - ግብር መሠረት በመተላለፊያ መሥመሮች ላይ በፌደራል ፖሊስ እና/ወይም በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚደረግ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ነው፡፡

12) "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን ቅ/ጽ/ቤቶችን ይጨምራል፡፡

13) "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ነው፡፡

14) በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ሌሎች ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ወደ ሀገር በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ፣ አገር አቋርጠው በሚሄዱ እና በአገር ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ትራንዚት ዕቃዎችና ማጓጓዣዎች እንዲሁም ከእነዚሁ ጋር ግንኙነት ባላቸው አስተላላፊዎች፣ አጓጓዦች እና ሌሎች ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

4. <u>መርህ</u>

1) የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት በዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና በሥጋት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት መሰረት ይከናወናል፣
2) የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃ ዋስትና እስከቀረበ ድረስ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ይጓጓዛል፣
3) ማናቸውም በትራንዚት የተመዘገበ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከመጀመሩ በፊት የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት ይፈፀምበታል፤
4) የትራንዚት ዕቃዎች በባለሥልጣኑ በተወሰነው የጉምሩክ መግቢያ ጣቢያዎች ወይም ወደብ በኩል በመግባት በተፈቀዱ የመተላለፊያ መስመሮች ዋናውን መንገድ ብቻ ተከትለው ይጓጓዛሉ፤
5) ማንኛውም የትራንዚት ዕቃ እንቅስቃሴው በሚያበቃበት የትራንዚት መዳረሻ ቦታ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ምዕራፍ አራት በተወሰነው ጊዜ እና ከጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ በተላከበት ሁኔታ መድረስ ይኖርበታል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የጉምሩክ ትራንዚት ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

5. <u>የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት</u>

1) በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዘዉ ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች ከአገር ዉስጥ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

ሀ/ እንደየሁኔታዉ IM4፣ IM5 ፣ IM6 ወይም IM7 ዲክለራሲዮን፣

ለ/ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ ወይም ለቀረጥና ታክሱ የተያዘ ዋስትና ወይም የቀረጥ ነፃ መብት ደብዳቤ፣

ሐ/ የማጓጓዣ ሰነድ፣

መ/ ዕቃው በኮንቴነር የመጣ ከሆነ የኮንቴነር ዋስትና፣

ሠ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል /ለ/ የተደነገገው ቢኖርም ቀረጥና ታክሱ ከተከፈለ ወይም

ዋስትና ከተያዘ በኋላ ዕቃው በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አገር ውስጥ ያልገባ ከሆነ የተሻሻለ ዲክላራሲዮን እና አዲስ የተሰላውን ቀረጥና ታክስ ወይም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል።

2) በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዘዉ ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች ከአገር ዉጭ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

ሀ/ ኮሜርሻል ኢንቮይስ/በባንክ የተረጋገጠ ፕሮፎርማ ኢንቮይስ ፣

ለ/ የትራንዚት ዲክለራሲዮን (IM8) እና (T1) ፣

ሐ/ የማጓጓዣ ሰነድ፣

መ/ ዋስትና

3) በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ተጓጉዘዉ ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

ሀ/ የትራንዚት ዲክለራሲዮን (IM8 እና T1)፣

ለ/ ዋስት፣

6. <u>የተላላፊ ዕቃዎች ትራንዚት (THROUGH TRANSIT)</u>

የተላላፊ ዕቃዎች የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

1) ዋስትና፣
2) ትራንዚት ዲክለራሲዮን (IM8)፣
3) ኮሜርሻል ኢንቮይስ፣
4) የማጓጓዣ ሰነድ፣

7. <u>የአገር ውስጥ ትራንዚት (INTERIOR TRANSIT)</u>

የአገር ውስጥ የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

1) ትራንዚት ዲክለሬሽን (IM8)፣
2) የማጓጓዣ ሰነድ፣
3) በመልቲ ሞዳል ተጓጉዞ የመጣ ዕቃ በስህተት የመድረሻ ጣቢያ ቀይሮ ከደረሰ እና የትራንዚት ክሊራንስ ተሰጥቶ ከሆነ ወደ ትክክለኛዉ የመድረሻ ጣቢያ ሲጓጓዝ ዋስትና፣

8. <u>የወጪ ዕቃዎች ትራንዚት</u>

የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፣

1) የወጪ ዕቃ የትራንዚት ዲክለራስዮን (EX8) እና (T1)፣

2) እንደአስፈላጊነቱ የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ፈቃድ ፣

3) የማጓጓዣ ሰነድ፣

## ምዕራፍ ሁለት

## የጉምሩክ ማሽጊያዎች እና ልዩ ምልክቶች

9. <u>የጉምሩክ ማሽጊያዎች ወይም ልዩ ምልክቶች መስፈርት</u>

ባለስልጣኑ የሚጠቀምባቸው የጉምሩክ ማሽጊያዎች ወይም ልዩ ምልክቶች እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፦

1) ጠንካራ አስተማማኝና ለረጂም ጊዜ የሚቆይ፣

2) በቀላሉ ለመቆለፍና ለማሸግ የሚቻል፣

3) በቀላሉ ለማንበብና ለመለየት የሚቻል፣

4) ካልተሰበረ ወይም ካልተነሳ በስተቀር እቃ ለማውጣትም ሆነ ለማስገባት የማያስችል፣

5) ከአንድ ጊዜ በላይ አገልግሎት የማይሰጥ (ኤሌክትሮኒክ ሲል ካልሆነ በስተቀር)፣

6) አስመስሎ ለመስራት የማይቻል፣

7) የጉምሩክ ማሸጊያ ወይም ልዩ ምልክት መሆኑን ለማመላከት በእንግሊዘኛ "CUSTOMS" የሚል ጽሑፍ የተጻፈበት፣

8) እሽጋ የሚያደርገዉ የቅጽ/ቤቱ ኮድና ተከታታይ ቁጥር ያለው፣

9) ለማሸግ ወይም ለመቆለፍ አመች የሆነ፣

10) አደጋን መቋቋም ከሚችል ማቴሪያል የተሰራ፣

11) ባለስልጣኑ ለዕቃው ደህንነት አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ሌሎች መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

10. <u>መታሸግ ያለባቸዉ ጭነቶች</u>

1) ማንኛውም የትራንዚት ዕቃ፦

ሀ/ በኮንቴኔር ወይም በባቡር ፍርጎ የተጫነ ከሆነ፣

ለ/ በሸራ ለማሸግ የሚመች ከሆነ፣

ሐ/ የነዳጅ ውጤቶች ከሆነ፣

በጉምሩክ ማሸጊያ መታሸግ ይኖርበታል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የትራንዚት ዕቃ በኮንቴነር ባይጫንም ወይም በሸራ ለመጫን ባይመችም በቀላሉ ሊሰበር፣ ሊቀሸብ፣ ሊለወጥ የሚችል ከሆነ እና አለም አቀፍ ስምምነት የማያስገድድ ከሆነ በ[illegible] ታሽጎ መጓጓዝ ይኖርበታል።

3) በውጭ ሀገር የጉምሩክ ሲል የታሸገ ጭነት እሽጉ በቂ ወይም አስተማማኝ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይም እሽጋዉን የሚያከናዉነዉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዕቃዉን ከመረመረ ጭነቱ በሲል ይታሸጋል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ መሰረት መታሸግ የሚገባቸው ዕቃዎች ለማሸግ የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ልዩ ምልክት ተደርጎባቸው እንዲጓጓዙ ሊደረግ ይችላል፡፡

11. <u>የማይታሸጉ ጭነቶች</u>

1) ከዚህ በታች የተመለከቱት የትራንዚት ዕቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ ሳይታሸጉ ሊጓጓዙ ይችላሉ፤

ሀ/ ትልልቅ የፋብሪካና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች፣

ለ/ የብረት ጭነቶች፣

ሐ/ ከኮንቴኔር ውጭ ተጭነው የሚመጡ ተሽከርካሪዎች፣

መ/ አስተማማኝና በቂ በሆነ ሁኔታ የታሸገና በባለስልጣኑ የማይመረመር በውጭ አገር ጉምሩክ ማሸጊያ የታሸገ ዕቃ፤

ሠ/ በባቡር የማይጫኑ የእርዳታ እህሎች፤የማዳበሪያ እና የድንጋይ ከሰል

ረ/ በግልጽ የሚታዩና ለትራንዚት ቁጥጥር አመቺ የሆኑ ጭነቶች፤

2) በአንቀጽ 10 የተደነገገው ቢኖርም የትራንዚት ሂደቱን ለማፋጠን የሚያግዝ ከሆነ፣ የአለም አቀፍ ስምምነት የሚያስገድድ ከሆነ እና የስጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑ ከታመነ ትራንዚት የሚያደርጉ ዕቃዎች በጉምሩክ ማሸጊያ ሳይታሸጉ እንዲጓጓዙ ሊደረግ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>የትራንዚት መግቢያ ወይም መነሻ ቦታዎች፣ የመተላለፊያ መስመሮች እና ማጠናቀቂያ ቦታዎች</u>

12. <u>የጉምሩክ ትራንዚት መግቢያ ወይም መነሻ ቦታዎች</u>

1) ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም የተላላፊ የትራንዚት ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መግቢያ ቦታ የሚሆኑት የጉምሩክ መግቢያ ጣቢያዎች ሆነው፡-

ሀ/ በጅቡቲ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ጋላፊ እና ደወሌ፣

ለ/ በሱዳን በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ሁመራ፣ መተማ ዮሐንስ፣ ማንኩሽ፣በሀምዛ ኩምሩክ/ጊዘን እና አልመሀል

ሐ/ በደቡብ ሱዳን ለሚገቡ ዕቃዎች - ቡርቤ፣መተሀር፣ላሬ/ፓጋግ እና ጊዘን

መ/ በኬንያ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ሞያሌ፣ ኦሞራቴ

ሠ/ በሶማሌ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ቶጉጫሌ፣ እንዲሁም

ረ/ ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው ሌሎች መግቢያ በሮች ናቸው፡፡

2) ከሀገር ለሚወጡ ወይም የአገር ውስጥ የትራንዚት ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ የሚሆኑት፡-

ሀ/ በመግቢና መዉጫ የሚገኙ የጉምሩክ ጣቢያዎች፣

ለ/ የተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን፣

ሐ/ ኢንዱስትሪ ዞን፣

መ/ በባለስላጣኑ የተፈቀዱ ሌሎች ቦታዎች ናቸው፡፡

3) ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም የተላላፊ የትራንዚት ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ የሚሆኑት፤

ሀ/ የጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት፤

ለ/ የበርበራ ማስተባበሪያ ጸ/ቤት፤

ሐ/ ባለስልጣኑ ወደፊት የሚወስናቸው ሌሎች የጎረቤት አገራት ወደቦች ናቸው፡፡

## 13. የጉምሩክ ትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታዎች

1) ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም የአገር ውስጥ ትራንዚት ለሚያደርጉ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታ የሚሆኑት በአንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ-መ) የተጠቀሱ ቦታዎች ይሆናሉ፡፡

2) በአንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ-ረ) የተዘረዘሩት የጉምሩክ መግቢያ ጣቢያዎች፣ ከሀገር ለሚወጡ ወይም ተላላፊ የትራንዚት ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታዎች ወይም መውጫ በሮች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

## 14. የመተላለፊያ መስመሮች

1) በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የትራንዚት ዕቃዎች የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡-

ሀ/ ጋላፊ ---> ሠመራ ---> ሚሌ ---> ገዋኔ ---> ገዳማይቱ ---> አዋሽ ---> መተሐራ ---> አዳማ ---> ሞጆ ---> አዲስ አበባ

ለ/ ጋላፊ ---> ሠመራ ---> ሚሌ ---> ገዋኔ ---> ገዳማይቱ ---> አዋሽ ---> መተሐራ ---> አዳማ ---> ሞጆ---> ሐዋሳ

ሐ/ ጋላፊ ---> ሰመራ ---> ሚሌ ---> ጭፍራ ---> ወልዲያ ---> አላማጣ ---> መቀሌ፣

መ/ ጋላፊ ---> ሰመራ ---> ሚሌ ---> ጭፍራ ---> ወልዲያ ---> ወረታ ---> ጉንደር

ሠ/ ጋላፊ ---> ሰመራ ---> ሚሌ ---> ጭፍራ ---> ወልዲያ ---> ወረታ ---> ባህርዳር

ረ/ ጋላፊ ---> ሰመራ ---> ሚሌ --->- ባቲ ---> ኮምቦልቻ

ሰ/ ጋላፊ ---> አፍዴራ ---> መቀሌ

ሸ/ ጋላፊ ---> አሳይታ

ቀ/ ደወሌ--------ድሬደዋ------ሐረር ---> ጅጅጋ

በ/ ደወሌ--->ድሬዳዋ ---> አዋሽ---- መተሀራ------አዳማ------ሞጆ-----አዲስ አበባ

ተ/ ደወሌ--->ድሬዳዋ ---> አዋሽ---- መተሀራ------አዳማ------ሞጆ-----አዋሳ

2) በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡-

ሀ/ ሞያሌ ---> ሜጋ ---> ያቤሎ ---> ሀገረማርያም ---> ዲላ ---> ሐዋሳ--- >ሻሸመኔ ---> ሞጆ ---> አዲስ አበባ (→ አዳማ)

ለ/ ኦሞራቴ ---> አርባምንጭ ---> ሻሸመኔ ---> ሞጆ ---> አዲስ አበባ (ሻሸመኔ → አዋሳ; ሞጆ → አዳማ)

3) በሱማሌ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከአገር ለሚወጡ የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡-

ሀ/ ቶጎጫሌ ---> ጅግጅጋ ---> ሀረር ---> ሚኤሶ ---> አዋሽ ---> አዳማ ---> ሞጆ ---> አዲስ አበባ

ለ/ ቶጎጫሌ ---> ጅግጅጋ ---> ሐረር ---> ድሬዳዋ ……> ደወሌ

4) በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡

ሀ) ሑመራ ---> ሽሬ ---> መቀሌ

ለ) መተማ ዮሐንስ ---> ጐንደር ---> ሽሬ ---> መቀሌ

ሐ) መተማ ዮሐንስ ---> ጐንደር --->ወረታ ---> ባህርዳር ---> አዲስ አበባ (ወረታ → ወልዲያ ---> ኮምቦልቻ)

መ) ሁመራ ---> ጐንደር ---> ወረታ --->ባህርዳር ---> አዲስ አበባ

ሠ) ማንኩሽ ---> ባህርዳር ---> አዲስ አበባ

ረ) በሀምዛ ---> ቻግኒ --->እንጂባራ --->አዲስ አበባ

ሰ) ማንኩሽ ---> ነቀምት ---> አምቦ --->አዲስ አበባ

ሸ) አልመሀል---> ማንኩሽ --->ቻግኒ ---> እንጂባራ --->አዲስ አበባ

ቀ) ጊዘን/ኩምሩክ---> አሶሳ ---> ነቀምት --->አምቦ --->አዲስ አበባ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

5) በደቡብ ሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡-

ሀ) መተሀር/ቡርቤ---> ጋምቤላ ---> ጅማ ---> ወሊሶ ---> አዲስ አበባ

ለ) ላሬ --->ጋምቤላ ---> ጅማ ---> ወሊሶ ---> አዲስ አበባ

6) አገር አቋርጠው ለሚሄዱ (ተላላፊ ትራንዚት) የመተላለፊያ መስመር የሚሆኑት፡-

ሀ) በሱዳን በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ዕቃዎች

1/ ሁመራ--> ሽሬ--> መቀሌ-->አላማጣ--> ወልዲያ--> ጥፍራ--> ሚሌ--> አዋሽ--> ሚኤሶ-->ደንገጎ-->ሐረር- -->ጅጅጋ--> ቶጎጫሌ

ሰመራ--> ጋላፊ

ድሬደዋ--->ደወሌ

ከ/ቻ-->አ.አ-->ሞጆ-->ሐዋሳ--->ሞያሌ

2/ መተማ ዮሐንስ--->ጉንደር---> ወረታ---> ባህርዳ ---> አ.አ ---> ሞጆ--->ሐዋሳ---> ሞያሌ

ወልዲያ-->ጭፍራ-->ሚሌ-->አዋሽ-->ሚኤሶ-->ደንገጎ-->ሐረር-->ጅጅጋ-->ቶጎ ጫሌ

ሰመራ --> ጋላፊ ድሬደዋ --> ደወሌ

ለ) በደቡብ ሱዳን የሚገቡ ወይም የሚወጡ ዕቃዎች

1/ ላሬ/መተሀር--> ጋምቤላ --> በደሌ--> ነቀምት--> አምቦ --> አ.አ

ጅማ ----> ወሊሶ----> አ.አ

2/ ጊዘን/ኩምሩክ--> አሶሳ--> ነቀምት--> አምቦ--> አ.አ

ሐ) በጁቡቲ በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ዕቃዎች

ወሊሶ --> ጅማ--> ጋምቤላ--> ቡርቤ/ፓጋግ/

አ.አ--> አምቦ--> ነቀምት-->አሶሳ--> ኩምሩክ/ጊዘን/

1/ ጋላፊ--> ሰመራ--> ሚሌ--> አዋሽ--> አዳማ--> ሞጆ--> ሐዋሳ --> ሞያሌ

ጭፍራ--> ወልዲያ--> አላማጣ--> መቀሌ--> ሽሬ--> ሁመራ

ወረታ--> ጎንደር--> መተማ ዩሀንስ

2/ ደወሌ--> ድሬደዋ --> አዋሽ--> መተሀራ--> አዳማ -->ሞጆ--> አ.አ-->ነቀምት-->አሶሳ--> ኩምሩክ/ጊዘን

ወሊሶ-->ጅማ -->ጋምቤላ-->ቡርቤ/ፓጋግ

መ) በሱማሌ በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ዕቃዎች

ቶጎጫሌ-→ ጅጅጋ-→ ሐረር -→ ደንገጎ-→ ድሬደዋ-→ ደወሌ

ሜኤሶ-→ አዋሽ-→ አዳማ -→ ሞጆ-→ ሐዋሳ -→ ሞያሌ

ሚሌ -→ ጭፍራ-→ ወልዲያ-→ አላማጣ -→ መቀሌ-→ ሽሬ-→ ሁመራ

ወረታ -→ ጎንደር -→ መተማ ዮሐንስ

ሠ) በኬንያ በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ ዕቃዎች

ሁመራ

1/ሞያሌ-→ ሐዋሳ-→ ሞጆ-→ አ.አ-→ ባህርዳር-→ ጎንደር-→ መተማ ዮሐንስ

አዳማ-→ አዋሽ-→ ሚኤሶ-→ ደንገጎ -→ ሐረር-→ ጅጅጋ-→ ቶጎጫሌ

ድሬደዋ-→ ደወሌ

ሚሌ---> ሰመራ---> ጋላፊ

ሁመራ

2/ ኦሞራቴ-→አርባምንጭ-→ ሻሸመኔ-→ ሞጆ-→ አዲስ አበባ -→ ባህርዳር-→ ጎንደር-→ መተማ ዩሀንስ

አዳማ-→ አዋሽ-→ ሚኤሶ -→ ደንገጎ-→ ሐረር-→ ጅጅጋ-→ ቶጎጫሌ

ድሬደዋ-----ደወሌ

ሚሌ-→ ሰመራ-→ ጋላፊ

6) በባቡር ተጭነው ለሚጓጓዙ ዕቃዎች የመተላለፊያ መስመር ተደርጎ የሚቆጠረው የባቡር መስመር የሚያልፍባቸው መስመሮች ናቸው።

## 15. የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች

1) በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የትራንዚት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚሆኑት፡-

ጋላፊ፣ ዲችኦቶ፣ ሰመራ፣ አሳይታ፣ ሚሌ፣ አዋሽ፣ ሞጆ፣ አቃቂ ቃሊቲ ፣ኮምቦልቻ፣ መቀሌ፣ ጐንደር፣ ባህርዳር፣ ሐረር፣ ጅጅጋ፣ ደወሌ፤በያቆቤ፤ዱሬ፤ደንበል፤

2) በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ፡-

ኦሞራቴ፣ ነገሌ ቦረና፣ ሞጆ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ሀዋሳ፣ ኮንሶ፣ ዶሎ ኦዶ፣ ሞያሌ፣ ያቤሎ፤ ሀገረ ማርያም፤ሻሸመኔ፤ አቦስቶ፤ አዳባ፤ጊነር

3) በሱማሌ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከአገር ለሚወጡ፡-

ቶጐጫሌ፣ጅጅጋ፣ሐረር፣ ደወሌ፣ ሜኤሶ፣ አዋሽ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣

4) በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ፡-

ሁመራ፣ ዲማ፤ ማይከድራ፤ ሉግዲ፤ መተማ ዮሐንስ፣ ማንኩሽ፣ አልመሃል፣ በሃምዛ፣ አብድራፊ፤ ገንዳውሃ፤ ሽንፋ፤ ኩምሩክ ፤ጊዘን፤መቀሌ፣

5) በደቡብ ሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ፡-

ጋምቤላ፣ አሶሳ፤ ላሬ፤ መተሀር፤ ጅማ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ መቀሌ፣ አዲስ አበባ

7) አገር አቋርጠው ለሚሄዱ የተላላፊ ዕቃዎች ትራንዚት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች የሚሆኑት በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 5 የተዘረዘሩት መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ይሆናሉ።

8) በባቡር ከሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ፡-

ደወሌ፣አይሻ፣አድጋላ፣ሀረዋ፣መልካጀብዱ፣ቢኬ፣ሜኤሶ፣ሲርባጉንጉር፣አዋሽ፣መተሐራ፣ፌጠ፣ አዳማ፣ሞጆ፣ቢሾፍቱ፣እንዶዴ፣ለቡ/ፋሪ፣ሰበታ

16. <u>ክልከላ</u>

ማንኛውም የትራንዚት ዕቃዎችን የሚያጓጉዝ አጓጓዥ በአንቀጽ 14 ከተዘረዘሩት የተፈቀዱ የመተላላፊያ መስመሮች እና በአንቀጽ 15 የተጠቀሱ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውጪ ማጓጓዣውን ማሳረፍ፣ ማቆም ወይም ማጓጓዝ የለበትም።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>የትራንዚት ጊዜ ገደብ</u>

17. <u>በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ የትራንዚት ዕቃዎች እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀን ገደብ</u>

ሀ) ከጋላፊ - አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት

ለ) ከጋላፊ - መቀሌ/ጉንደር/ባህርደር <u>አራት</u> ቀናት

ሐ) ከደወሌ - ጅጅጋ <u>ሁለት</u> ቀናት

መ) ከጋላፊ - ሐዋሳ <u>ሦስት</u> ቀናት

ሠ) ከደወሌ - ሐዋሳ <u>ሦስት</u> ቀናት

ረ) ከደወሌ - አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት

ናቸው።

18. <u>በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀን ገደብ</u>

ሀ) ከሞያሌ - አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት

ለ) ከኦሞራቴ --- አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት ፣

19. በሱማሌ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከአገር ለሚወጡ እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ

ሀ) ከቶጎ ጫሌ - ድሬዳዋ ሁለት ቀናት

ለ) ከቶጎ ጫሌ - አዲስ አበባ አራት ቀናት

20. በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ

ሀ) ከሁመራ- መቀሌ ሁለት ቀናት

ለ) ከመተማ ዩሐንስ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት

ሐ) ከሁመራ - አዲስ አበባ አራት ቀናት

መ) ከማንኩሽ/አልምሀል/በሀምዛ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት

ሠ) ከመተማ ዩሐንስ - መቀሌ ሁለት ቀናት

ረ) ከኩምሩክ/ጊዘን - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት

ሰ) ከመተማ ዮሐንስ - ኮምቦልቻ ሁለት ቀናት

ሸ )ከመተማ ዩሐንስ- ጎንደር አንድ ቀን

ቀ) ከበሀምዛ/አልምሀል - ባህርዳር ሁለት ቀናት

በ) ከመተማ ዩሐንስ - ባህርዳር ሁለት ቀናት

21. በደቡብ ሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ

ሀ) ላሬ/መተሀር/ቡርቤ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት

22. አገር አቋርጠው ለሚሄዱ እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ

ሀ) ከሁመራ ---- ጋላፊ አምስት ቀናት

ለ) ከሁመራ --- ቶጎጫሌ ሰባት ቀናት

ሐ) ከሁመራ ---- ሞያሌ ስድስት ቀናት

መ) ከመተማ ዮሐንስ ---- ጋላፊ አምስት ቀናት

ሠ) ከመተማ ዮሐንስ ---- ቶጎጫሌ ሰባት ቀናት

ረ) ከመተማ ዮሐንስ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት

ሰ) ከቶጎጫሌ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት

ሸ) ከደወሌ ---- ቶጎጫሌ ሦስት ቀናት

ቀ) ከጋላፊ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት

በ) ከጋላፊ -------በሀምዛ/አልመሀል ስድስት ቀናት

## ክፍል ሶስት

## የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት የሚያከናውኑ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### ምዕራፍ አንድ

### የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ ክፍሎች ተግባርና ኃላፊነት

23. የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታዎች /ጣቢያዎች/ ኃላፊነት

1) የዲክላራሲዮን አቅራቢው የትራንዚት ፈቃድ ሲጠይቅ ለትራንዚት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች ስለመቅረባቸው፣ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸዉ እና የተያዘዉ ዋስትና በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2) የዕቃዉን ትክክለኛነት ሲጫን በአካል ተገኝቶ በማረጋገጥ በሲል ማሸግና ሲል ቁጥሩን በአውቶሜሽን ሲስተም በመመዝገብ የትራንዚት ፈቃድ (T1) አዘጋጅቶ በመስጠት ትራንዚቱ እንዲጀምር መፍቀድ፣
3) ትራንዚት የጀመሩ ጭነቶች መረጃ ወደ መረጃ ቴክኖሎጂ ቋት የማስተላለፍ፣
4) የዕቃ መያዣው ወይም ማጓጓዣው የታሸገበት የጉምሩክ ማሸጊያ የተፈታ ወይም የተነሳ ወይም የተቀየረ እና ከትራንዚት ዕቃዎች ላይ ዕቃ ለመቀነስም ሆነ ለመጨመር የተደረገ ህገ-ወጥ ድርጊት ስለመፈፀሙ የሚያስረዱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ካረጋገጠ ወይም በቂ ጥርጣሬ ካደረበት የዕቃ መያዣውን ወይም ማጓጓዣውን በጣቢያው የጉምሩክ ማሸጊያ በማሸግ በፌደራል ፖሊስ እና/ወይም እንደአግባብነቱ በባለሥልጣኑ የህግ ማስከበር አባል/ኦፊሰር ታጅቦ ወደ ትራንዚት መድረሻ ጣቢያው እንዲጓጓዝ የማድረግ፣
5) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25(4)፣28(3) እና 29(1) መሰረት የመድረሻ ጣበያ ለወጥ ሲያጋጥምና ጥያቄው ሲቀርብለት የመድረሻ ጣቢያ የመቀየር (re-route) ኃላፊነት አለበት::

24. በጉምሩክ ትራንዚት መተላለፊያ መስመር የሚገኙ ጣቢያዎች ኃላፊነት

1) ዕቃው ከመነሻ ጣቢያ የትራንዚት ፈቃድ የተሰጠዉ መሆኑን የማረጋገጥ፤
2) በተፈቀደለት መስመር መጓጓዙን የማረጋገጥ፤
3) በተነሳበት ሁኔታ የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ ትራንዚት ሂደቱን እንዲቀጥል መፍቀድ፣
4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንኡስ አንቀጽ 4 ላይ የተጠቀሱ ተግባርና ኃላፊነቶች ማከናወን::

25. የጉምሩክ ትራንዚት ማጠናቀቂያ ቦታዎች /ጣቢያዎች/ ኃላፊነት

1) ጭነቱ በተነሳበት ሁኔታ ስለመድረሱ የማረጋገጥ፤
2) በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ ትራንዚቱን ማጠናቀቅ፣

3) በጊዜ ገደቡ የደረሱና ያልደረሱትን በሲስተም የማጣራትና የማስታረቅ (Reconcilation) ሥራ መስራትና በጊዜ ያልደረሱትን ወደ ህግ ማስከበር በማስተላለፍ ክትትል እንዲደረግባቸዉና ያስያዙት ዋስትና ለባለስልጣኑ ገቢ እንዲሆን ማድረግ፣
4) ከአጓጓዡ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ምክንያት መንገድ በመዘጋቱ፣ ወደብ ከአቅም በላይ በመጨናነቁ፣ እና ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ሲያጋጥም እና ጥያቄዉ ትራንዚቱ ከመተናቀቁ በፊት የቀረበ ከሆነ መድረሻ ጣቢያ በመቀየር የደረሰ እንደሆነ አዲሱ መድረሻ ጣቢያ ለመነሻ የጉምሩክ ትራንዚት ቅ/ጽ/ቤት የመድረሻ ጣቢያ ቅያሬ (re-route) እንዲደረግለት የማሳወቅ፣
5) በዚህ መመሪያ መሰረት ታጅበው የመጡ ዕቃዎች የደረሱበትን ሁኔታ እና ያለውን ልዩነት አጀባ ላደረገው ቅ/ጽ/ቤት በጽሁፍ የማሳወቅ፣
6) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ትራንዚት የሚያደርጉ ዕቃዎች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልደረሱ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ገቢ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 26. የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ተግባርና ኃላፊነት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ባለስልጣኑ ትራንዚት የሚያደርጉ ዕቃዎች እንዲታጀቡ ሲጠይቅ ያጅባል፣
2) በመተላለፊያ መስመሮች ላይ የጉምሩክ ትራንዚት ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀምን ተላልፈው በፓትሮሊንግ ቡድን የሚያዙ ማጓጓዣዎችን እና እቃዎችን ከመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ዕቃውን ከነማጓጓዣው አጅቦ የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታ ያደርሳል፤
3) ከዋናው መንገድ የሚወጡትንና ባልተፈቀደላቸው ቦታ የሚቆሙትን ማጓጓዣዎች አጅቦ ለሚቀጥለው ጣቢያ ያስተላልፋል።
4) የፌዴራል ፖሊስ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ተግባራት እንደ አግባብነታቸው የክልል የፀጥታ ወይም ህግ አስከባሪ አካላትን በማሳተፍ ሊያከናውን ይችላል።

### 27. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

1) በመልቲ ሞዳል የትራንዚት አገልግሎት አማካኝነት ለሚያስመጧቸው ዕቃዎች በቂ የሆነ የአንድ ዓመት የኢንሹራንስ ወይም የባንክ አጠቃላይ ዋስትና ማቅረብ፣

2) የወደቦቹና ተርሚናሎቹን ዓቅም ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው አጠቃላይ ቦንድ ለቅ/ጽ/ቤቶች ከፋፍሎ ማስያዝ፣

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ማስያዝ የሚገባው የቀደመ አጠቃላይ ቦንድ ያስያዘው ከማብቃቱ አንድ ወር ቀደም ብሎ ይሆናል፣

4) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28(2) እና 29(1) እና (4) የተገለጹት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በአቅራቢያው ለሚገኝ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ህግ አስከባሪ አካል በነዚህ ድንጋጌዎች በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ውስጥ የማሳወቅ ግዴታ አለበት::

## ምዕራፍ ሶስት

## የዲክላራሲዮን አቅራቢ፣ የማጓጓዣ ኃላፊ እና የቦንድድ መጋዘን ባለቤት ተግባርና ኃላፊነት

### 28. የማጓጓዣ ኃላፊ ኃላፊነት

ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ:-

1) ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠውና የጉምሩክ ሹም በሥፍራው ሳይኖር ወደ ሀገር የሚገባን ወይም ከሀገር የሚወጣን ተላላፊ ዕቃ እና ማጓጓዣ ከተወሰነው የጉምሩክ ወደብ ወይም የመተላለፊያ መስመር ውጪ ማንቀሳቀስ፣ ማቆም፣ ዕቃ መጫን ወይም ማራገፍ፣ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውንም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ መፍቀድ፣ ወይም ማሳፈር፣ የጉምሩክ እሽጐችን መፍታት፣ ማላቀቅ፣ መሥበር ወይም መቀየር ወይም እነዚሁ ህገ-ወጥ ተግባራት በሌሎች ሰዎች እንዲፈፀሙ ማድረግ የለበትም ነው::

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ማጓጓዣው ከተወሰነው የጉምሩክ ወደብ ውጪ ሊቆም ይችላል:: ሁኔታዉ ሲያጋጥመዉ በአቅራቢያው ለሚገኝ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል በ24 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ አለበት::

3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ አጓጓዡ ለመነሻና ለመድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ እንዲሁም ለዲክላራሲን አቅራቢው በ 8 የስራ ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ አለበት::

### 29. የዲክላራሲዮን አቅራቢ ኃላፊነት

ማንኛውም ዲክላራሲዮን አቅራቢ:-

1) ከመነሻ የጉምሩክ ትራንዚት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተፈቀደው የመዳረሻ ጣቢያ በመንገድ ብልሽት ወይም ሌላ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር እና የማዳረሻ ጣቢያ ለማስቀየር (re-rout) ከፈለገ ለመነሻ ጣቢያ ጥያቄውን አቅርቦ ማስፈጸም፣

2) ትራንዚት ፈቃድ የሚጠይቅ ከሆነ DTIን በመጠቀም በጉምሩክ አውቶሚሽን ሲስተም

የትራንዚት ዲክላሬሽን መሙላት፣

3) ለትራንዚት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አሟልቶና ትክክለኛነታቸውን አረጋግጦ ለጉምሩክ በማቅረብ የትራንዚት ፈቃድ መጠየቅ፣

4) የትራንዚት ፈቃድ ተሰጥቷቸዉ በጊዜ ያልደረሱ ጭነቶች ካሉ በ8 የስራ ሰዓት ውስጥ ለመድረሻ የጉምሩክ ጣቢያ በመቅረብ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

5) ቀረጥና ታክሱ ከተከፈለ ወይም ዋስትና ከተያዘ በኋላ ዕቃው በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አገር ውስጥ ያልገባ ከሆነ የተሻሻለ ዲክላራሲዮን እና አዲስ የተሰላውን ቀረጥና ታክስ ወይም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

30. የቦንድድ መጋዘን ባለቤት ኃላፊነት

ማንኛውም የቦንድድ መጋዘን ባለቤት የትራንዚት ዕቃ ተጓጉዞ ወደ መጋዘኑ ሲደርስ ዲክለር ላደረገበት ቅ/ጽ/ቤት ዕቃው የደረሰ መሆኑን በሁለት ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ ይኖረበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

31. የዋስትና ዓይነት

1) ዲክለራሲዮን አቅራቢዉ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸዉ ትራንዚት በማድረግ ወደ አገር ለሚገቡ ዕቃዎች የጥሬ ገንዘብ ፤ የባንክ ጋራንቲ ወይም የኢንሹራንስ ቦንድ አንዱን መርጦ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም የተመረጠው ወሰትና ከሚፈጸመው የጉምሩክ ስነስርአት አፈጻጸም ጋር የማይጣጣም ከሆነ የተመረጠውን ዋስትና ውድቅ በማድረግ የባንክ ጋራንቲ እንዲያቀርብ ያስገድደዋል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገዉ ቢኖርም በመንግስት በጀት ሙሉ በሙሉ የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት በፁሑፍ የተደረገ ስምምነት ማቅረብ ይችላል፡፡

32. ለህዝብ ስለማሳወቅ

ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ መሠረት የተወሰኑ የመግቢያና የመውጫ በሮች፣ ማቋረጫዎች እንዲሁም የመተላለፊያ መስመሮች በአዋጁ አንቀጽ 140 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በህዝብ ማስታወቂያ ይገልጻል፡፡

33. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

1) የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 16/2001

2) የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ (ማሻሻያ) ቁጥር 39/2002 እንዲሁም

3) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮች እና የአሠራር ሥርዓቶች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

34. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ 12/09 ቀን 2008 ዓ.ም

አብርሃም ንጉሴ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር